መስከረም 29 ቀን 2006

# ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ከጥቅምት 1 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ.ም እንደሚካሄድ መገለጹ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም በተጠቀሰው ቀን ምዝገባውን ለመጀመር የሚያስችል የምዝገባ ማስፈጸሚያ መመሪያና ሌሎች አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ባለመጠናቀቃቸው የምዝገባው ቀን እንደተራዘመ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ስምምነት ላይ መደረሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አሳውቋል፡፡

በዚሁ መሠረት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ከህዳር 1 እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሚካሄድ መሆኑን እያሳወቅን፤ መመሪያው እንደደረሰን የምዝገባ መስፈርቶቹን የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ ቶኪዮ

Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia TOKYO